መጽሐፈ ሜላድ

መቅድም

ይኽ መጽሐፈ ሜላድ በደጉና ጻድቁ
ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ
መንግሥት የቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ
ሊቃውንት ተሰብስበው በጊዜው
የእመቤታችንንና የቅዱሳንን አማላጅነትና
ለእነርሱም የሚገባውን ስግደትና አክብሮት
በመቃወም ለተነሣው አባ እስጢፋኖና
ተከታዮቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ለመስጠት
ከብሉያትና ከሐዲሳት አውጣጥተው
አሰባስበው የጻፉት ቅዱስ መጽሐፍ ነው።

መጽሐፉ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን
እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ
ዓለም ከባህርይ አባቱ **እግዚአብሔር አብ** ያለ
እናት ድኅረ ዓለምም ከእመቤታችን **ድንግል
ማርያም** ያለ አባት ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ
ነፍስ የነሣበትን ነገረ ልደቱን ምሥጢረ
ሥጋዌውን አምልቶ አስፍቶ ያስረዳል።

Scanned with ACE Scanner

ሥጋዌውን አምልቶ አስፍቶ ያስረዳል።

ምሥጢረ ሥላሴንም ተንትኖ እያስረዳ በዘመናችን ለሚነሡ ጥያቄዎችም በቂ መልስነት ያላቸውን የእመቤታችንና የቅዱሳንን አማላጅነትና አዳኝነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች ከነትርጓሜያቸው በመግለጽ ለእነርሱም የአክብሮትና የጸጋ ስግደት እንደሚገባቸው ከብሉያትና ከሐዲሳት እየጠቀስ የሚያስረዳ እጅግ ታላቅና ጥልቅ ትርጓሜያትን የያዘ መጽሐፍ ነው።

ስያሜ ርእሱም ሜላድ ተሰኝቷል ሜላድ የሚለው ዘርአ ቃልም አለደ አከማቸ፤ ሰበሰበ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው። ከዚኹ ግእዛዊ አንቀጽም በዋድላዊውና ዋሽራዊው የግሥ ርባታ ጥልቅ የምርምር አገላለጽ ሒደት መሠረት ሜላድ ምዕላድ ዐላድ ሌድ ሉውድ የሚሉ ባእድ ዘሮችና ውስጠ ዘርአች ይረባሉ ይወጣሉና ።

በዚኽም መሠረት ይኽ መጽሐፍ ሜላድ የተሰኘበት ምሥጢረ ሥላሴንና ምሥጢረ ሥጋዌን እያስረዳ ስለ እመቤታችንና ስለ ቅዱሳን ኹሉ አማላጅነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ

Scanned with ACE Scanner

በዚኽም መሠረት ይኽ መጽሐፍ ሜላድ የተሰኘበት ምሥጢረ ሥላሴንና ምሥጢረ ሥጋዌን እያስረዳ ስለ እመቤታችንና ስለ ቅዱሳን ኹሉ አማላጅነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃወችን ከነትርጓሜያቸው ይሰጥ ዘንድ በሊቃውንተ ኢትዮጵያ ከብሉያትና ከሐዲሳት ተውጣጥቶ በታላቁ ደገኛው ጻድቅ ንጉሥ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ስለ ተጻፈ ነው። ሜላድ ማለት ከላይ እንደተጠቀሰው ክምችት ስብስብ ማለት ነውና ።

በቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ከ፲፬፻፸ወ፬ ዓም እስከ ፲፬፻፷ የነገሠው ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ከአራቱም ማዕዘን የሰበሰባቸው ሊቃውንትን ጉባኤ ሠርቶ ወንበር ዘርግቶ በጊዜው ተነሥተው ከነበሩ ተሐድሶውያንና መናፍቃን አይሁድና አሕዛብ ጋራ በማ ከራከርና በመዳኘት መሠረታዊው አስተምህሮተ ሃይማኖት በሕገ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እየተገለጸና እንዲህ በመጽሐፍ ተጽፎና ተጠብቆ ይኖር ዘንድ ታላቅ መንፈሳዊ ተጋድሎን የፈጸመ ርቱዐ ሃይማኖት ንጉሥ ነው።

Scanned with ACE Scanner

ይኽ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ
ወላጆቹ ለእመቤታችን ድንግል ማርያም
በገቡት ብፅዐት በፈቃደ እግዚአብሔር
የተወለደ የስእለት ልጅ መኾኑ ይታወቃል።
ከፍጹም ክርስቲያን ቤተሰብእ የተገኘ ፍጹም
መፍቀሬ እግዚአብሔር ስለ ነበረም
ከብላቴንነቱ ጀምሮ እስከ መዋዕለ ሕይወቱ
ፍጻሜ ድረስ እመቤታችንን እመ አምላክ
ልጇ ወዳጇ መድኃኔዓለም ኢየሱስ
ክርስቶስንም አምላክ ወልደ አምላክ እያለ
ሲመሠክር ሲያስተምር በጉባኤ ሲከራከር
ሲያከራክር መኖሩን እጅግ ብዙ ቅዱሳት
መጻሕፍት ይመሠክራሉ።

ከአምላክ እስራኤል እግዚአብሔር ክብር
መገለጥ የተነሣ በወዳጁ ነቢይ ሙሴ ፊት ላይ
የተሳለውን የብርሃን ጸዳል ያዩ ሕዝበ
እስራኤል ተገልበብ ለነፊትህን ሸፍነህ
ተናገረን እስኪሉት ድረስ ለሕገ እግዚአብሔር
ቀናዒ በነበረው ነቢይ ሙሴ ላይ ነፀብራቃዊ
የብርሃን ጐርፍ እንደፈሰሰበት ኹሉ ስለ
አጋእዝተ ዓለም ሥሉስ ቅዱስ አንድነት
ሦስትነት በመሠከረና በመዋዕለ መንግሥቱ
ኹሉ ስለ ርትዕት ሃይማኖት በቁና በዘኹ

Scanned with ACE Scanner

ሦስትነት በመሠከረና በመዋዕለ መንግሥቱ ኹሉ ስለ ርትዕት ሃይማኖት በቀና በዚኹ ጻድቅ ንጉሥ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብም ዘመነ መንግሥትም በፈቃደ እግዚአብሔር ከሰማይ የብርሃን ጐርፍ ፈስሷል ።

በርኅርኅተ ልብ እመቤታችን አማላጅነትና ተራዳኢነት ብርሃን የፈሰሰባት ብርሃን የወረደባት ሥፍራም ልዩ ስሟ ኤባ ትሰኛለች ለእመቤታችንና ልጇ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ለተሰቀለበት ቅዱስ መስቀል አንሰግድም ብለው በጊዜው ተነሥተው የነበሩና አይሁዳዊ ኑፋቄን የተሸከሙ መናፍቃን በጉባኤ ተወግዘው ከተለዩ ከሠላሳ ስምንት ቀን በኋላ መጋቢት ዐሥር ቀን ብርሃን ወረደ ።

ብርሃኑም በንጉሡ አደባባይና ከንጉሡ አደባባይ እስከ ሩቅ ሥፍራዎች ኹሉ በእየሰዉ ልብስ ኹሉ ላይ በእየዕቃውም በእየአብያተ ክርስቲያናቱና በንዋያተ ቅድሳቱ ኹሉ ላይ ፈሰሶ ይታይ ነበር። ብርሃኑም የእሳት ላንቃ ይመስላል አይፋጅም ይልቁንም የዐረፈበትን ኹሉ እያበራ ደስ ያሰኘዋል እንጂ

Scanned with ACE Scanner

የዐረፈበትን ኹሉ እያበራ ደስ ያሰኘዋል እንጂ በንጉሡና በባለሟሎቹ በሕዝቡም ኹሉ ዘንድ ታላቅ ደስታ ኾነ ንጉሡ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብም ጥንት ኤባ የተባለች ያችን ሥፍራ ደብረ ብርሃን ብሎ ሰየማት ።

በዚኽም መሠረት የሠራዊት ጌታ ልዑል እግዚአብሔር ለወዳጁ ነቢይ ሙሴ በነፀብራቀ በርሃንና በወጀቦ መኻል ለነቢዩ ኤልያስም በቀጤን የድምፅ ፋፃ ዐውሎ ነፋስ ውስጥ ክብሩን እንደ ገለጸ ኹሉ ስለሕጉ ለሚቀኑ ወዳጆቹም ኃይለ ፍቅሩን ጸጋ ረድኤቱን በአምሳለ ትዕምርተ ብርሃን እንዲህ ይገልጻልና። እንግዲህ ደጋግመን ከላይ እንደገለጽነው ለብርሃን ልጇ ክርስቶስ ክቡር መስቀልና ለእናቱ እመብርሃን ድንግል ማርያም መስገድን ለአልወደዱ ከሃድያንና እነርሱን መስለው እስከ ፍጻሜ ዘመን ለሚነሡ የዲያብሎስ የግብር ልጆች መናፍቃን ኹሉ በቂና ተገቢ የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ የአለበት። ይኽንን መጽሐፈ ሚላድ በእመቤታችን አማላጅነት በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ በጥንታውያኑና

እግዚአብሔር ፈቃድ በጥንታውያኑና እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ሊቃውንት አንደበትና ብዕር የአስገኘልን ይኸው ታላቁ ጻድቅ ርቱዐ ሃይማኖት ንጉሥ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ነው።

ይኸው መጽሐፈ ሚላድ በእየወሩ የመግቢያ መጀመሪያ ንባበ አንቀጽ **ንጽሕፍ ድርሳነ ልደቱ ለአምላክነ ፤ንጽሕፍ ድርሳነ ልደቱ ለእግዚእን፤ ንጽሕፍ ድርሳነ ልደቱ ለፈጣሪነ** ይላል ዳግመኛ በእየማዕከሉ በሚገኙ አዝርእተ ንባባትም ድርሳነ ልደቱ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ **ኢየሱስ ክርስቶስ** እንዲል የጌታችንና የመድኃኒታችን የአምላካችን **ኢየሱስ ክርስቶስን** ነገረ ልደቱን የሚናገር ድርሳንነቱንም ያበሥራል። እንኪያስ ይኸው መጽሐፈ ሚላድ **ድርሳነ እግዚአብሔር ወልድ** ተብሎ የተሰየምም መኾኑን ልብ ይሏል።

መጽሐፈ ሚላድ ወይንም ድርሳነ **እግዚአብሔር ወልድ** ተብሎ በሚታወቀው በዚኽ መጽሐፍ ውስጥም *ርኢኬ ኦ ንፉቅ ርጉም ፀረ ማርያም ከመ ኢተጎጉለ ምስሌከ ሰሎሞን ጠቢብ ዘይቤ ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ*

Scanned with ACE Scanner

መጽሐፈ ሜላድ ወይንም ድርሳነ
እግዚአብሔር ወልድ ተብሎ በሚታወቀው
በዚኽ መጽሐፍ ውስጥም ርኢኬ ኦ ንፉቅ
ርጉም ፀረ ማርያም ከመ ኢተጎጉለ ምስሌከ
ሰሎሞን ጠቢብ ዘይቤ ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ
እግዚአብሔር እስመ ነሥሐ እምአበሳሁ
ዘገብረ ቀዲሙ ወተነበየ ትንቢተ በእንተ
ማርያም ድንግል ዘወላዲት አምላክ መድኃኔ
ኵሉ ዓለም ወይቤ ንኢ ጎቤየ ርግብየ
ሠናይትየ ፍጽምትየ እስመ አልብኪ ነውር
ወኢምንትኒ በላዕሌኪ ገነት ዕፁት ዐዘቅት
ጎትምት ፍናወ ዚአኪ የሚል ገጸንባብ በገጽ
፴፫ አንቀጽ ፴፬ ላይ ይገኛል ።

ትርጉሙም አንተ ርጉም ፀረ ማርያም
መናፍቅ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን
መፍራት ነው። ያለ ጠቢቡ ሰሎሞን ከአንተ
ጋራ እንዳልተጐዳ አስተውል አስቀድም
ከሠራው ስህተቱ ተመልሶ ንሥሓ ገብቶ
ፍጽምት ድንግል የምትኾኝ መልካሚ ርግብ
ድንግል ሆይ ወደእኔ ነይ ምንም ምን ነውር
የሌለብሽ የታጠረች የተክል ቦታ የተቈለፈች
የውኃ ምንጭ አንቺ ነሽ እያለ የዓለሙን
መድኃኒት አምላክን ስለወለደች ድንግል

Scanned with ACE Scanner

መድኃኒት አምላክን ስለወለደች ድንግል ማርያም ትንቢት ተናግሯልና ማለት ነው።

የዓለሙን መድኃኒት አምላክ ወልደ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደች የእመቤታችን ተዐምር በዓለም ዙሪያ ኹሉ ይነገር ይታወቅ ዘንድ በውጪ በእየዓለማቱ ያለውን ተዐምራን ወደሀገር ውስጥ እያስመጣ በሀገር ውስጥም የተደረገውን ተዐምሯን ወደውጪ እያለከ ለዓለም በማዳረስ ለእመብርሃን ወላዲተ አምላክ የአለውን ጽኑዕ ፍቅሩን የገለጸው ርቱዐ ሃይማኖት ኢትዮጵያዊው ጻድቅ ንጉሥ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ይኽ መጽሐፈ ሚላድ ወይም ድርሳነ እግዚአብሔር ወልድ የተጻፈበትን ምክንያት በእየዐሥራ ኹለቱም ወራት የእየንባባቱ መደምደሚያ ላይ በሚደንቅና በተመሳሳይ አንድ ዐይነት ገጸ ንባብ ደጋግሞ ገልጾታል ። በዚኽም ሳያበቃ ይኽ መጽሐፈ ሚላድ ወይም ድርሳነ እግዚአብሔር ወልድ የተጻፈበት ምክንያቱን በዚኽ መጽሐፍ ኅትመተ ገጽ ሦስት የግእዝ አዕማድን በሚመላ ገጸ ንባብ ለዐሥራ ኹለተኛ ጊዜ በሰፊው ገልጾልናል።

Scanned with ACE Scanner

ይኽ መጽሐፈ ሜላድ ወይም ድርሳነ እግዚአብሔር ወልድ በአለው መንፈሳዊና ሰማያዊ ልዕልና ኢትዮጵያውያን በሚረዱበት የዕለት ተዕለት ቋንቋቸው ይተረጉምላቸው ዘንድ ሲሹት ኑረዋል። በዓለም ዙሪያ የአሉ የእምነት ሊቃውንትና ልዩ ልዩ የመንፈሳዊ ታሪክ ተመራማሪዎችም ሲኾኑ በልዩ ልዩ ቀደምት ጊዜያት በእየቋንቋቸው ተርጒመው ለዓለም ለማበርከት ሞክረዋል።

ለምሳሌም ያህል ኩርት ቬንት የተባለው የውጭ አገር መተርጒም በ፲፱ወ፷፪ -- በ፲፱ወ፷፫ አከታትሎ ከጀርመነኛ ትርጒሙ ጋራ ከአሳተማቸው ኢትዮጵያውያን ቅዱሳት መጻሕፍት መኻል አንደኛው ይኸው ድርሳነ እግዚአብሔር ወልድ የተሰኘው መጽሐፈ ሜላድ እንደነበር አንድ አንድ የሀገራችን ሊቃውንት ሳይቀሩ ብዕራቸው እየጻፈ ቃላቸው እየመሠከረ የሚታይ የሚሰማበት የዘመናችን የሥነ ጽሑፍ በጎ ክሥተት ላይ እንገኛለን።

Scanned with ACE Scanner

ነገር ግን ትክክለኛውንና ጥንታዊውን የግእዝ
ዘርአ ንባብና የፍቺውንም አመሥጥሮተ
ትርጓሜ በትክክል ለማግኘትና ለመውረስ
የራሳችንን ቅዱሳት መጻሕፍት ምዕራባውያኑ
ከእኛው ወስደው ለእኛ የሚሰጡንን ዝርውና
ድሙር ትርጓሜ ኹሉ እንደው በዘፈቀደ
ከመቀበል ይልቅ የሊቃውንት ጉባኤ አባል
እንደኾኑት እንድ መልዐከ ሰላም ቆሞስ አባ
ቴዎድሮስና የቅኔና የትርጓሜ መምህር
እንደኾኑት እንደ ሊቀጉባኤ ታረቀኝ ደምሴ
የትርጓሜ በቂ ልምድና ሙያ በአላቸው
በሀገራችን ቀለማውያን ሊቃውንት በራሳችን
ነቢበ ፍካሬ በራሳችን የአተረጓጎም ብሂለ
ልሳን የተተረጕሙና የራሳችንን ኢትዮጵያዊ
ጣዕመ ሐተታ የተጐናጸፉ ጥንታውያን
ቅዱሳት መጻሕፍቶቻችን እንዲህ በእየጊዜው
እየታተሙ መቅረባቸው እጅግ ደስ የሚያሰኝ
ኢትዮጵያዊ ዕሜት ያለው ግሩም ጸጋ ነው።

Scanned with ACE Scanner